# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 54

የካቲት 19 ቀን 2015ዓም (26-02-2023)

የዚህ ሳምንት ቅንብራችን ካለፈው ብዙ ባይለይም እንግዳ ሆኖ ብቅ ያለው ብልጽግና በሚል ቅርጫት ውስጥ ከተጠቀጠቁት የጥፋት ሃይሎች መካከል በኦህዴድና በባአዴን ዙሪያ እውነት ይሁን ለማስመሰል የተከፈተው የቃላት ጦርነት ግርምትን ፈጥሯል።ከዚያ በፊት ግን አንዳንድ እርእሶችን እናነሳለን።

በወለጋም ሆነ በአዲስ አበባ ዙሪያ ሲደረግ የቆዬው አማራውን የማፈናቀል ተግባር በስፋት ቀጥሏል። በወለጋ አማራዎች በኦሮሙማው ግንባር ስር በተሰለፈ ከኦነግ፣ከኦሕዴድ፣ከልዩ ሃይል፣ከሚሊሽያ፣ ከአገር መከላከያም ጭምር የተውጣጣ ጦር በክልሉ ይኖሩ በነበሩት የአማራ ተወላጆች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋና ማፈናቀል መፈጸሙን ቀጥሎበታል።ከዚያም ውጭ በአማራው ክልል በሰሜን ሸዋ ተመሳሳይ ወንጀል በመፈጸሙ ብዙዎች ሲሞቱ ሌላው ማምለጥ የቻለው በያቅጣጫው ተበታትኖ ሜዳ ላይ ፈሷል።ለርሃብና ለበሽታ ተጋልጦ የእርዳታ ያለህ እያለ በመጮህ ላይ ነው።

በአብይ አህመድ የሚመራው የኦሮሙማው ቡድን ባለው አገር የማዋለድ ህልሙና እቅዱ የተነሳ እንቅፋት ይሆናሉ ያላቸውን ዜጎች በተለይም አማራውን ለማጥፋት የጭካኔ እጁን በሁሉም አቅጣጫ ከዘረጋ ውሎ አድሯል።በአዲስ አበባ ውስጥ ለዘመናት የኖሩትን ዜጎች ለወደፊቱ ሸገር በሚል ስም የኦሮሚያ ከተማ እመሰርታለሁ በሚል ቅዠት ቤታቸውን አፍርሶ መድረሻ ያሳጣቸውን ለመቁጠር ያዳግታል። በኢትዮጵያ የሰው ልጅ በገዛ ሃገሩ፣በመንግሥትህ ነኝ ባይ አካል መኖሪያ ቤቱ እዬፈረሰ ስደተኛ ሲሆን በታሪክ ይህ የመጀመሪያው ነው።በነበሩት ሥርዓቶች የነዋሪው ቦታ ለመንግሥት የግንባታ ሥራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ቤት ከመፍረሱ በፊት ነዋሪው እንዲዘጋጅ የጊዜ ገደብ ተቀምጦ፣ ለቦታውና ለቤቱ ግምት መክፈል ወይም ተቀያሪ ቤት ወይም ቦታና የቤት መሥሪያ ካሳ መስጠት የተለመደ አሠራር ነበር።በኦነጋውያኑ የሥልጣን ዘመን ግን እንኳንስ ካሳና ተቀያሪ ሊሰጠው ቀርቶ ከዱላና ከጥይት መስተንግዶ አልዳነም።ባለፈው ሳምንት ቅንብራችን ዘጠኝ ህጻናት በጅብ መበላታቸውንና ተስፋ በመቁረጥ ህይወታቸውን ያጠፉ መኖራቸውን ገልጸን ነበር፤አሁንም ተመሳሳይ ሁኔታ የተከሰተበት ሳምንት ነው።ለአይምሮ መቃወስ የተዳረጉም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። በመጠለያ እጦት ላይ የምግብ እጦት ሲጨመርበት የሚደርሰውን ጉዳት ሲያስቡት ይዘገንናል።ይህ ሁሉ በደል የሚደርሰው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ነው።የሌላውም ጎሳ ተወላጅ ኢትዮጵያ አገሩን እንዲጠላ ያልተደረገ ሴራ የለም።እምቢ ያለው የኦሮሞም ተወላጅ ቢሆን በኦሮሙማው ቡድን ዓይን ጠላት ተደርጎ ይቆጠራል፤የተገደሉትም ቁጥራቸው ብዙ ነው።ምንም ይሁን ምንም ኢትዮጵያዊነትን ከኢትዮጵያውያን ልብና አይምሮ የሚፍቅ ሃይል አይኖርም፤ከንቱ ድካም ነው።ይዋል ይደር እንጂ የኦሮሙማውና የህዋሀታውያኑ አገር አፍርሶ አገር የማዋለድ ዓላማ ተጨናግፎ ወንጀለኞቹ ለፍርድ የሚቀርቡበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም፤ለዛም ማሳያዎች ብቅ ብቅ እያሉ ነው። ያ ጊዜ እንዲመጣ ግን የሕዝቡ በአንድ ላይ መቆምና መታገል ወሳኝ ነው።

በወያኔና በኦነጋውያኑ መካከል ተደረሰ የተባለው ስምምነት በመሸራረፍ ላይ ነው።መተማመን የለም። ሁለቱም የመሬት ቅርምት ግብግብ ውስጥ ገብተዋል።ወያኔ የአማራውን መኖሪያ አጽመ እርስቶች ራያና ወልቃይትን ለመንጠቅ ጦሩን እያሰማራ በአንዳንድ ቦታዎችም ላይ ይዞታውን እያጠናከረ ለወሳኝ

ጦርነት በዝግጅት ላይ ይገኛል።አነጋውያኑም የሰፌ መሬት ባለቤት ለመሆን የሁሉንም ክልል ድንበር እዬጣሱ በመውረር ካርታ በመንደፍ ላይ ናቸው። በታሪክ ጠላት ነው ብለው ከመደቡት የአማራ ክልል በተጨማሪ ከሶማሌ፣ከአፋር፣ከሲዳማ፣ከደቡብ፣ከጋምቤላ፣ከቤንሻንጉል ክልሎች ጋር  በመሬት ወረራ ውዝግብ ገብቶ ሁሉም የተቃውሞ ድምጹን እያሰማ ነው።ሁሉም ኬኛ በሚል በሽታ የታወረው ቡድን ለስግብግብነቱ ድንበር የለሽ ሆኗል።በዚህ ላይ የምቀኝነት፣የበታችነትና የበቀል ስሜት ሲጨመርበት ከሰው ተራ ወጥቶ አውሬ  አድርጎታል።ሁሉ አማረኝን ገበያ አታውጧት እንደሚባለው በግርግር ሥልጣኑን በመያዛቸው መዝረፉንም፣መሸቀርቀሩንም፣ያዩትን ሁሉ ይኑረኛ ባይነቱንም  የተለዩ ችሎታ አድርገው ይቆጥሩታል እንጂ ከደካማነት የመነጨ መሆኑን አልተረዱም።ዱሮም ቢሆን መረዳት የሚችል አይምሮ መች ፈጠረባቸውና! በዬቀኑ የሚቀበሩበትን ጉድጓድ እንደሚቆፍሩ  አልታያቸውም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ለማፈራረስ የተወጠነው ሴራ በሕዝቡ አንድነትና ተቃውሞ በመክሸፉ የተደናገጠው ቡድን ከአፈርኩ አይመልሰኝ በሚል ቁጭትና ንዴት በሚወስደው እርምጃ  ማንነቱ ይበልጥ ገሃድ እዬወጣ መጥቷል። አብይ አህመድ ሕገወጡን የሳውሪዎስን ቡድን ለማባረር ከሕጋዊው ሲኖዶስ ጋር የገባውን ስምምነት ለመፈጸም ሳይችል ቀርቶ ሕገ ወጦቹን ባሉበት ቦታ እንዲቀመጡ አድርጓል።በወለጋም ውስጥ  በአንዳንድ ቦታዎች ብቸኛ የቤተክርስቲያን ተጠሪ በመሆን በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው።ተመልሰዋል የተባሉትም በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ባይታወቅም  ከቀሩት ጋር ከውስጥና ከውጭ ሆነው በማፍረሱ ሥራ ላይ እንደተጠመዱ መገመት አያቅትም።ዝምታውም ለዚያ ማረጋገጫ ሆኗል።የኦነጉ ተጠሪ አብይ አህመድ ካለው ፍላጎትና የማሸከርከር ልምዱ አንጻር የነሳዊሪዎስ ቡድን  ነገ ተመልሶ አካኪ ዘራፍ የማይልበት ምክንያት የለም።አድፍጦ ጊዜ የሚጠብቅ እንጂ ከልቡ ንስሃ ገብቶ የመመለሱ ነገር አጠራጣሪ ነው።

የኦሮሙማው ቡድን  በሚከተለው ኋላ ቀር ፖለቲካና አልጠግብ ባይነት በገጠመው ሕዝባዊ ተቃውሞ ከደረሰበት መንገጫገጭና የመፈራረስ አደጋ ለመዳን በልዩ ልዩ ስም የሚንቀሳቀሰው የኦነግ ቤተሰብ አንድ ላይ ለመሰባሰባሰብ በመጠራራት ላይ ነው።በተለይም በአማራው በኩል የሚታዬው እምቢ ባይነት እንቅልፍ ነስቶታል።ይይዝ ይለቀው ግራ ገብቶታል።በአንድ በኩል ወታደራዊ ሃይሉን እያሰባሰበና መሬት እዬነጠቀ በሌላ በኩል የኤኮኖሚ እድገት አምጥቻለሁ፣ለብዙ ዜጋ የሥራ ዕድል ከፍቻለሁ የሚል ፕሮፓጋንዳ ይነዛል።መሬት ላይ የሚታዬው ግን የዚያ ተጻራሪ ነው። በክፍለሃገር ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ በቀን አንድ ዳቦ ገዝቶ ለመብላት የተራራ መውጣት ያህል አዳጋች የሆነበት ዜጋ ቁጥሩ ትንሽ አይደለም። የመብራትና የውሃው ነገርማ አይነሳ!ከአፍሪካ በኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጨት የመጀመሪያውን ቦታ የያዘችው አገራችን ሕዝቧ በከተማም ሆነ በገጠር በጨለማ የሚዳክርባት ፣በውሃውም በኩል የብዙ ወንዞችና ጅረቶች፣የአባይ ወንዝ መነሻ የሆነችው አገር ሕዝቧ በውሃ ጥም የሚያልቅባት አገር ሆናለች። የኦሮሙማው ቡድን ግን መብራቱንም ውሃውንም ለጎረቤት አገራት እዬቸበቸበ ዶላር ይሰበስባል፤በውጭ አገር ቅንጡ ቤትና ንብረት ይገዛበታል።

በጣም የሚገርመው ነገር በአገር ደረጃ እንኳንስ ለዳቦ ፋብሪካ ቀርቶ በቤተሰብ  ምጣድ ላይ ለሚጋገር ቂጣ እንኳን የሚሆን የስንዴ ዱቄት ለማግኘት አዳጋች ሆኗል።ፋብሪካዎች ለመዝጋት በተገደዱበት ጊዜ ኢትዮጵያ ከራሷ አልፋ ለጎረቤት አገሮች ስንዴ ላከች የሚለው ተረት ተረት መስማቱ የሥርዓቱን ምንነት ይበልጥ አጋልጦታል።አብይ አህመድ ከራሱ ሕዝብ አልፎ ሌላውን ዓለም በተለይም አፍሪካን ለማታለል መድፈሩ የሰውዬውን የአይምሮ ጤንነት ከጥያቄም አልፎ የሚያረጋግጥ ሆኗል።በሚሊዮን የሚቆጠር ዜጋ በርሃብ አለንጋ እዬተገረፈ፣የውጭ እርዳታ በሚጠዬቅበት አገር ስንዴ ለውጭ አገር ተላከ የሚለው ወሬ ሲሰማ ለጆሮ ይከብዳል።ነገሩን ይበልጥ የተለዩ የሚያደርገው በአገር ውስጥ

ተመረተ የሚባለው አነስተኛ የስንዴ ምርት እንኳ ለሕዝቡ ሳይሆን ለአብይ አህመድ የአፍ ወለምታ መሸፈኛ እንዲሆን ገበሬው በግዳጅ ለመንግሥት በርካሽ ዋጋ እንዲሸጥ መደረጉ ነው።

በአገሪቱ የገበያ ተመን በ4,000-4,500 ብር መሸጥ የነበረበት መቶ ኪሎ ስንዴ ለመንግሥት በ3,250ብር እንዲሸጥ በመገደዱ፣ገበሬው ላለመሸጥ በመወሰኑ በተፈጠረው እጥረት የዋጋ ግሽበት አስከትሏል።ከስንዴ ምርት ጋር የተያያዙት የፋብሪካ ውጤቶች በእጥፍ ተወደዋል።አንድ ኪሎ ማካሮኒ ከ40 ብር 80 ብር ገብቷል፤በዚህም ዋጋ ቢሆን ለማግኘት አስቸጋሪ ነው።ሌላውንም በዚህ መልኩ መገመት ይቻላል። እንደ ውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬ የስንዴውም የጥቁር ገበያው ተስፋፍቷል።ስንዴ ይዞ ኬላ ለማለፍ በዬኬላው የሚከፈለው ጉቦ የስንዴውን ዋጋ እጥፍ አድርሶታል።ለመክፈል ያልቻለው ደግሞ ከመወረስ ባለፈም ቅጣት ይጣልበታል። ለምሳሌም በናዝሬት ከተማ በአለፉት ቀናት መቶ ኪሎ ስንዴ ከ5,500 ብር በላይ በጥቁር ገበያ ተሽጧል፤በዚህ ሳይቆም እዬጨመረ እንደሚሄድ ስጋት አለ። በኦሮሚያ ክልል በበቦረና ውስጥ ሕዝብ በርሃብ እንደ ቅጠል እዬረገፈ፣እንስሳቱም መንምነው እዬሞቱ ባሉበት ሁኔታ ለኦሮሞ ሕዝብ ሙብት ቆሜያለሁ ብሎ ሥልጣን ላይ ያለው አነጋዊ ቡድን በራሱ ሕዝብ አስከሬን ላይ ዶላር እሰበስባለሁ ብሎ ስንዴ እዬነጠቀ ለውጭ አገር መቸብቸቡን መርጧል። የጭካኔውን ደረጃ ያሳዬበት ደግሞ የቦረና ሕዝብ እርሃብና እልቂት አጀንዳዬ አይደለም የሚል ትእቢትና ክህደት የተመላበት መልስ መስጠቱ ነው። እርዳታ ቢመጣም ከሕዝቡ ነጥቆ የፖለቲካው ማራምጃና የገንዘብ ጥማቱን መወጫ ከማድረግ እንደማይመለስ በተደጋጋሚ ታይቷል ተፈጥሮውም ሰብአዊነትን አይፈቅድለትም። የሰው ልጅ ጥንስስ ከማህጸን ዘንጥሎ የሚያወጣ ጨካኝ የኦሮሙማ ቡድን ለቦረና ሕዝብ ያስባል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው።ወይም የቡድኑን ምንነት አለማወቅ፣አለያም በጥቅማጥቅም ተገዝቶ ገበናውን ለመሸፈን መሞከር ነው።እዬጮኸ ያለው ሌላው አገር ወዳድና የእርዳታ ድርጅቶች ናቸው።የነዚህን ጥሪ ሰምቶ ለሚያደርጉት ሰብአዊ ድጋፍ ሁሉም እንዲተባበር xri እናደርጋለን።

ላለፉት 32 ዓመታት አብሮ አገር ሲንድና ሲበዘብዝ ከነበረው አጋሩ ከብአዴን ጋር በቃላት እዬተጨፋጨፈ ይገኛል።እስተ አገባው ለይምሰል ይሁን ከእውነት የምናዬው ይሆናል።የኦሮሙማው መሪ አብይ አህመድ በብአዴን በኩል የመጣበትን ተቃውሞ ለማሶገድ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸውን እነአገኘሁ ተሻገርን ያካተተ የሽግግሌ ቡድን በመላክ ቢሞክርም በቀላሉ የሚወጣው ጉዳይ አልሆነም። ተቃውሞው የአማራውን ተወላጅ ሁሉ ያካተተ ስለሆነ የኢሕአዴግ አመራር በቀላሉ ሊቆጣጠረው ቀርቶ እራሱንም ለማዳን ከማይችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ይመስላል። አብይ አህመድ በሃይልም ለማንበርከክ ኮማንዶ መላኩ ተሰምቷል።በኤኮኖሚም የሕዝቡን ትኩረት ለማስለወጥ በቀን 300 ሽህ ዳቦ የሚጋግር ፋብሪካ በጎንደር ተከፈተ የሚል ወሬ ይዞ በሚስቱ በዝናሽ በኩል የሚመራ ቡድን ለምረቃ ስነስርዓት ልኳል።የጎንደር ሕዝብ ጥያቄው ከዳቦ ፋብሪካ በላይ ነው፤በዚህ አይጭበረበርም። አዲስ አበባም ከሚሊዮን በላይ ዳቦ የሚጋግር ፋብሪካ ተከፈተ ተብሎ ወሬው ከጆሮ ሳይጠፋ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል።የጎንደሩም ከዚያ የተለዬ ዕድል ይገጥመዋል አንልም።ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ እንዲሉ የፈረንጅ ዳቦ መግመጡ፣ፓስታና መኮሮኒ በሹካ መጠቅለሉ ቀርቶበት የነጭ ጤፍ ሳይሆን የገብስ ወይም የማሽላ እንጀራውን የመቁረሱ ጸጋ ቢኖረው ተመስገን ይል ነበር።ለም አገር ይዞ እርሃብና ቸነፈር ቅስም የሚሰብር ፣ ብሔራዊ መታወቂያ መሆኑ እንኳንስ ኢትዮጵያውያኑን መመላውን የጥቁር ሕዝብ ያሳፍራል።ከዛም በላይ በጎሳ እዬተጨፋጨፉ አገርን ያህል ትልቅ የጋራ ይዞታ ለማፈራረስ መሽቀዳደሙ የዓለማችን አሳፋሪና አስፈሪ ታሪክ ሆኗል።

የወልቃይትና የራያ ጉዳይ አሁንም ለአማራው ሕዝብ የፖለቲካው ማጠንጠኛ ነው።ወያኔና ኦነግ በአንድ ላይ ከአማራው እጅ ለመንጠቅ በጥምረት በመሥራት ላይ ናቸው።ከደቡብና ከሰሜን በመከበብ

አማራውን ፋታ ለመንሳት የሚያደርጉትን ወረራ በመናበብ ስኬታማ ለማድረግ በሁሉም አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው።በነ ኮሎኔል ደመቀ የሚመራውን ኮሚቴ ለማፍረስ ያልተሞከረ ሙከራ የለም።አሁንም አልቆመም።ቢቻል በስምምነት ካልተቻለም በሃይል ለማስፈጸም ቆርጠው ተነስተዋል። አማራውም እንዲሁ ወልቃይትና ራያ ወይም ሞት ብሎ አሻፈረኝ ብሏል።የብአዴን መፈተሻው በዚህ ጥያቄ ላይ የሚወስደው አቋም ነው። ከአዛዡ ከኦሮሙማው ቡድን መሪ ከአብይ አህመድ ትዕዛዝ ማፈንገጡን በቃላት ሳይሆን በተግባር ማሳዬት አለበት።እስከ አሁን ድረስ በስርዓቱ ላይ ያሰማው ተቃውሞ የለም።አሁንም ቤሔር ብሔረሰቦች በሚለው ኧላቀር የጎሳ ፖለቲካ ውስጥ እዬዳከረ ነው። ደጋግሞ ያማራው ጠላት እያለ ቢናገርም ማን እንደሆነ ደፍሮ አልገለጸውም።ለዚያም ነው አካኪ ዘራፉ ከልብ ነው ወይስ ለማስመሰል የሚደረግ የማጭበርበር ጊዜ መግዣ ያልነው።ሌላው መለኪያው በኦሮሙማው ትዕዛዝ በእስር ቤት ያጎራቸውን የፋኖና የልዩሃይል አባላት መፍታት አንዱና ቀዳሚው ተግባር ነው።በዚህ ጥያቄ ላይ ክፍልፍል እንደተፈጠረ ሰምተናል።በነ ግርማ የሽጥላ የሚመራው የኦነግያውያኑ ተላላኪ ክንፍና ሌላው ከእንቅልፉ በነቃው የባእዴን አባል መካከል ልዩነት መኖሩና በሁለት ጎራ መሰለፉ የተሰማ ሲሆን ልዩነቱ በንግግር ሳይሆን መሣሪያ ያማዝዛል የሚል ስጋት አሳድሯል።እኛም ከወያኔና ከኦነጋውያኑ ጋር በንግግር የሚፈታ ችግር እንደማይኖር እናምናለን። ስለሆነም ሁሉም ይዘጋጅ እንላለን።

በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ት/ቤቶች በማናለብኟ በአዳነች አቤቤ ትዕዛዝ የኦሮምኛ ቋንቋ ትምህርት መጀመሩን ሰምተናል። ግዳጁ በግል ትምህርት ቤት ባሉትም ላይ ከአንድ እስከ ሶስተኛ ክፍል የተጣለ ሲሆን ትምህርት ቤቶቹ ምንም አይነት ዝግጅት ሳይደረግ እንዴት ይሆናል ቢሉም ትዕዛዙን ካልፈጸሙ እንደሚዘጉ አዳነች አቤቤ አስጠንቅቃለች። ቋንቋ መማሩ ጉዳት ባይኖረውም ሰፊ ዝግጅትና የተማሪውን ፈቃደኛነትና ፍላጎት ይጠይቃል።መማር ያልፈለገ ያለመማር መብቱም ሊከበርለት ይገባል። በእብሪት የሚጨኑት ግዳጅ ሊሆን አይገባም።ሌላው ትልቁ ነጥብ የትምህርት ስርዓቱ አንድ ወጥና አገራዊ መልክ መያዝ ሲገባው ማንም እንዳሻው የሚያቦካው ከሆነ ለትምህርቱ ጥራት ማጣትና ለተማሪውም የእውቀት ደረጃ አለመመሳሰል ምክንያት ይሆናል።በዚያ መልክ የታነጸው ትውልድ አገር የሚገነባ ሳይሆን እንደ አሁኑ መሪዎች አገር የሚያፈርስ ይሆናል።የኦሮሙማው ቡድን ግን ትኩረት የሰጠው ለትምህርቱ ጥራት ሳይሆን ኦሮሙማን የሁሉም ነገር የበላይና አድራጊ ፈጣሪ በማድረጉ ላይ ነው።

በበጋ ያበደ በክረምት ልብሱን ይቀዳል እንደሚባለው ሁኔታውን ተረድተው አደብ ለመግዛት ያልቻሉት ኦነጋውያን እውነትም የእብድ ፖለቲካ የማራመዳቸው ነገር ከቀናት በኋላ በይካቲት 23 ቀን ለሚከበረው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ያደረጉት ዝግጅት ሌላውን ቀርቶ በስሙ የሚነግዱበትን ማህበረሰብ ያሳፈረና ያዋረደ ነው።ሲጀመር በአድዋ ድል አያምኑም፤የሚጠሉት ምንሊክ የመራው በመሆኑ ከጣሊያኖች በላይ ይጠሉታል።ለነሱ ጀግና ማለት ከኢትዮጵያም አልፎ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝብ፣በቅኝ አገዛዝ ሥር ለወደቁት ሁሉ የነጻነት ምሳሌ የሆነውን ጦርነት የመራው ምኒሊክ ሳይሆን በጎሳ ነጻ አውጭነት የተሰለፈ ጸረ አንድነት የሆነ አሸባሪ ግለሰብ ወይም ቡድን ነው። የሚኒሊክ ሃውልትን አፍርሰው ለዚህ አይነቱ ጎሰኛ ሃውልት ማቆምን ይመርጣሉ።ያም በመሆኑ ነው በአድዋ ድል መታሰቢያ ላይ የድሉ ባለቤት የሆኑትን አጼ ሚኒሊክና እቴጌ ጣይቱን ከታሪክ ቦታቸው አውርደው በጊዜውና በቦታው መኖር ቀርቶ ያልተወለደ፣የአርባ አምስት ዓመት ዕድሜ ያለውን የኦነጋውያኑን መሪ አብይ አህመድን የአድዋ ጀግና አድርገው ለማቅረብ በመዘጋጀት ላይ ናቸው። ለማጭበርበርም በአጼ ሚኒሊክ ጦር ውስጥ ተሰልፈው በጀግንነት የተዋጉትንና ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ክብር ሲሉ ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡትን የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑትን ባለውለታ የደጃዝማች ባልቻ አባጣፎን ምስል በመጨመር ከታሪክ ሽሚያ ላይ ገብተዋል።የበዓሉ ባለቤት ሕዝቡ ሳይሆን

የኦሮሙማ ቡድን የሚያሽከረክረው መከላከያ ነው ተብሏል።የምንሊክ ስም ሲነሳና አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሲያይ ዛሬ የሚቀሰቀሰውና የሚያንቀጠቅጠው የኦነጉ ቀጃላ መርዳሳ የሚመራው የባህልና ቱሪዝም መሥሪያ ቤት ይህንን ዝግጅት በግንባር ቀደምተኝነት እዬመራው ይገኛል። መከበር ከሚኖርበት ከምኒሊክ አደባባይ ወስዶም በመስቀል አደባባይ ለማድረግ ወስኗል።ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ የተፈጸመ ሲሆን የሕዝቡና በተለይም የወጣቱ ተቃውሞ የሚዘነጋ አይደለም።በዚያን ጊዜ ከተቃወሙት መካከልም ብዙ ወጣቶች ተገለዋል፤ቴዲ ቡና አንዱ ነው።ዘንድሮ ተመሳሳይ ተቃውሞ እንዳይነሳ ወጣቱ በገፍ በመታፈስ ላይ ነው፤ግን ሁሉንም ወጣት አፍሰው አይጨርሱትም።ካለፈው በበለጠ ሕዝቡና ወጣቱ ወጥቶ ይቃወመዋል የሚል ግምት አለን።እኛም የታሪክ ቀበኛ ታሪክ አያውቅም፤የሚያኮራ ታሪክም አይሠራም እንላለን።

በትናንትናው በቅዳሜው እለት የሰማነው አስደንጋጭ ዜና አባልደራስ ለእውነተኛ ፓርቲ መስራችና ሊቀመንበር የነበረው እስክንድር ነጋ በባሕርዳር እስርቤት ውስጥ መኖሩን ነው።ከዓመት በፊት የት እንደገባ ያልታወቀውና በብዙዎች በኩል ገዳም ገባ፣ፋኖን ተቀላቀለ የሚል መላ ምት ሲነገርበት የነበረው እስክንድር የመታሰሩን ወሬ ስንሰማ ፣በህይወት በመኖሩ ደስተኞች ስንሆን በእስር ቤት መገኘቱ ግን ትንሽ ቅስማችንን እንደሰበረው መደበቅ አንሻም።የመሰረተው ድርጅት ብዙ ማድረግ በሚጠበቅበትና ውዥንብር ውስጥ ሲገባ በቅርበት ሆኖ አመራር መስጠት ነበረበት የሚል ቀና ምክር ነበረን።መታሰሩ ላይቀር ምንም እንኳን የእስራት ልዩነት ባይኖርም በሚያውቀው ሕዝብና፣ በታገለለት ከተማ ቢሆን ይሻል ነበር እንላለን።እሱ ከራቀ በኋላም ነው ድርጅቱ ውስጥ ውዝግብና መከፋፈል መኖሩ የታወቀው።አሁንም በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚታወቅ የለም።ለማንኛውም እሱና ሌሎቹ በፍጥነት እንዲፈቱ መታገል የሁሉም ለውጥ ፈላጊ ግዴታ ነው።የአንጋፋው ታዲዎስ ታንቱና የሌሎቹም ጉዳይ እንዳይረሳ አሁንም እንደሁሌዬው ጥሪ እናደርጋለን።

የአነጋውያኑና የህውሃታውያኑ አገር የማፍረስ ሴራ ይከሽፋል!!

በሕዝባዊ ትግሉ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም!!

ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!